የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን

ሰንበት ትምህርት ቤቶች መሠረታዊ ትምህርት

በሕጋዊው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ቅዱስ ሲኖስ ስር የሰንበት ትምሕርት ቤቶች አንድነት ጉባኤ

ማውጫ

ማንኛውም ክርስቲያን ሊያውቀው የሚገባ የእምነት መሠረት የሆነው የእምነት መግለጫችን ..... - 1 -

ጸሎተ ሃይማኖት፡ ..... - 1 -

ነገረ ሐይማኖት፡ አእማደ ምሥጢር ..... - 1 -

ምሥጢረ ሥላሴ፡ ..... - 1 -

ሚሥጢረ ሥጋዌ፡ ..... - 2 -

ሚሥጢረ ትንሣኤ ሙታን፡ ..... - 3 -

ነገረ ቤተክርስትያን፡ ..... - 4 -

ሚሥጥራተ ቤተክርስትያን ..... - 5 -

ሰባቱ ሚሥጢራተ ወይም ሥራዓተ ቅዳሴ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤ ..... - 5 -

ሀ. ሥርዓተ ጥምቀት ..... - 5 -

ሚሥጢረ ጥምቀት፡ ..... - 5 -

ሚሥጢረ ሜሮን፡ ..... - 6 -

ሚሥጢረ ቁርባን፡ ..... - 6 -

ሚሥጢረ ክህነት፡ ..... - 7 -

ሚሥጢረ ንስሐ ..... - 8 -

ሚሥጢረ ቀንዲል ..... - 9 -

ሚሥጢረ ተክሊል ..... - 10 -

ክብረ ቅዱሳን ..... - 11 -

አምልኮ፥ ጾም፥ ጸሎት፥ እና ባሕላት ..... - 11 -

አምልኮ ..... - 11 -

ጾም ..... - 12 -

ጸሎት ..... - 12 -

ባእላት ..... - 13 -

ሥርዓተ ቤተክርስትያን ..... - 14 -

ክርስትያናዊ መብትና ግዴታ ..... - 14 -

<u>ማንኛውም ክርስቲያን ሊያውቀው የሚገባ የእምነት መሠረት የሆነው የእምነት መግለጫችን</u>

ጸሎተ ሃይማኖት፡

ታሪካዊ አቀማለጡ ምንም እንኳ መናፍቃንን ለመለየትና ምእመናንም በትክክለኛው ሃይማኖት እንዲጸኑ ለማድረግ ታስቦ በጉባኤ ኒቂያ በ325 ዓ.ም እና በጉባኤ ቁስጥንጥንያ በ381 ዓ.ም የተወሰነ ቀኖና (ሕገ) ሃይማኖት ቢሆንም የትምህርቱ ይዘት ግን ከጥንት ጀምሮ በጌታ እና በሐዋርያት ትምህርት ውስጥ ነበር። ጥንት ቤተ ክርስትያን ሳትከፋፈል እና አባቶችም ሳይወጋገዙ በጎብረት እና በአንድነት በሚሠሩበት ጊዜ የነበሩ መንፈሳውያን መሪዎችና ሊቃውንት አባቶች ይህንን ጽሎተ ሃይማኖት ከቅዱሳት መጻሕፍት አወጣትተው በ12 አንቀጾች ከፍለው በማዘጋጀት የክርስትና መሠረተ እምነት ሆኖ እንዲሠራበት በውሳኔአቸው ለአብያተክርስትያናትና ለምእመናን ሁሉ አስታውቀዋል አውጀዋልም።

<u>ነገረ ሐይማኖት፡ አእማደ ምሥጢር</u>

ነገረ ሃይማኖት ወይም አምስቱ አእማደ ምሥጢር ማለት ማንኛውም ክርስትያን ሊያውቀው ወይም ሊማረው ½Q| መሠረታዊ የሃይኖት ትምህርት ነው። እነርሱም ፤

1. ምሥጢረ ሥKg
2. ሚሥጢረ ሥጋዌ
3. ሚሥጢረ ጥምቀት
4. ሚሥጢረ ቁርባን
5. ሚሥጢረ ትንሣኤ ሙታን

<u>ምሥጢረ ሥላሴ፡</u>

የማይታይና የማይመረመር ሁሉን ማድረግ የሚችል የሚታየውንም የማይታየውንም ፍጥረት ሁሉ የፈጠረ ይቅርታው ቸርነቱ ያልተወሰነ ለዘላለም የሚኖር መጀመሪያው እና መድረሻው የማይታወቅ የማይመረመር ልዑል እግዚአብሔር አምላካችን የሚግልጠውና ራሱን የገለጸው በሥሉስ (ሶስት) አካላት (ህላዊነት) እና በዋሕድ መለኮት(በአንድ) መለኮት ነው። እነዚህም እንዲህ ተብለው ይገለጣሉ

- የአካል ህላዌያት(የኩነታት) ስሞች፤ አብ፣ ወልድ፣ መንፈስ ቅዱስ።
- የአካላት የግብር ስም፤ አብ፡ ወላዲ፣ ወልድ ፡ ተወላዲ (ልጅ)፤ መንፈስ ቅዱስ፡ ሠራጺ ።

በስም፣ በአካል፣ በግብር ሦስት ቢባሉም በመለኮት (በአምላክነት)፣ በሥልጣን፣ በአገዛዝ፣ በህልውና፣ በባሕርይ፣ በህልውና፣ በልብ፣ በቃል፣ በእስትንፋስ አንድ እግዚአብሔር ብለን እናምናለን።

በአካል ሦስት ማለት፤

- አብ፤ ሁለንተናዊ ፍጹምና ምሉዕ አካል፣ ያለው። ሲሆን አብ ማለትም አባት ማለት ነው።

- ውልድ፤ ፍጹም ምልዕ ሁለንተናዊ አካል ያለው ሲሆን። ወልድ (ቃል) ማለትም ልጅ ወይም የአብ ቃል ማለት ነው።
- መንፈስ ቅዱስም፤ ፍጹም ምሉዕ ሁለንተናዊ አካል፣ ያለው ሲሆን መንፈስ ቅዱስ ማለት ሠራዒ ማለት ነው።

በግብር (በሥራ) ሦስት ናቸው ማለት፤

- የአብ ግብር (ሥራ) መውለድ እና ማስረጽ | የውልድ (የቃል) ግብር (ሥራ) መወለድ | የመንፈስ ቅዱስ ግብር (ሥራ) መሥረፅ ነው።

አብ ቢወልድ ቢያሠርጽ እንዲ አይወለድም አይሠርፅም። ወልድም ቢወለድ እንጂ አይወልድም አያሠርፅም። መንፈስ ቅዱስም ቢሠርፅ እንጂ አይወልድም አያሠርፅም።

ሥላሴ በአካል፣ በግብር፣ እና በስም ሦስት በመለኮት፣ በስልጣን፣ በአገዛዝ አንድ ከሆኑ ይህንን አለም እንዴት ፈጠሩት?

- አብ ልብ በመሆን ይህንን አለም አሰበ ወልድ ቃል በመሆን ይህንን አለም ይኩን ብሎ ተናገረ መንፈስ ቅዱስ ሕይወት በመሆን ይህንን አለም ሰራ። በሌላ አነጋገር አብ በራሱ አምሮ ይህንን አለም አሰቦ በውልድ ቃልነት ተናግሮ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ይህንን አለም ፈጠረ። ወልድም በአም አምሮ አሰቦ በራሱ ቃልነት ተናግሮ በመንፈስ ቅዱስ ሕይወትነት ይህንን አለም ፈጠረ። መንፈስ ቅዱስም በአብ አምሮ አሰቦ በወልድ ቃልነት ተናግሮ በራሱ ሕይወትነት ይህንን አለም ፈጠረ ብለን እናምናለን። እንዲህ አድርጎ ማስቀመጥ ይቻል ይሆን ሦስቱ የሥላሴ አካላት ልባውያን ነባብያን መስተን ፍሳን ለእነዚህ የእግዚአብሔርውያን አካላት ለአያንዳንዳቸው ያላቸው አሳቢ ልብ ነባቢ ቃል ሕያዊ መስትንፍስ አላቸው አንልም ሁሉም አንድ ልብ ያስባሉ ብአንድ ቃል ይናገራሉ ብአንድ ሕያው መስተንፍስ ሕያው ሁነው ይኖራሉ
- **የ ሥላሴ ሚሥጢነት ትርጉም**

ማንኛውም በዓለመ መንፈስ ወይም ብአግዚአብሔርዊ ባሕርይ የሚገለጥና የሚጠና ቅድስናን ገላጭ የሆነ ጥናት ሁሉ ምሥጢር የሚል ስያሜ ይሰጣዋል ይኸም ከሁለት አቅጣጫ ይታያል አንደኛው ከሰው አዕምሮ ውሱንነት ሲሆን ሁለትኛው ከቅዱሱ እግዚአብሔር ቅድስና የተንሣ ይሆናል

ግ የእግዚአብሔር ሦስትነት እና አንድነት በሙላት ለመረዳት የሰው ልጅ አዕምሮ የግንዛቤ መጠኑ እጅግ አናሳ ስለሆነ ምስጢር ተባለ። ይህም የተሸሸገ ለማለት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ርቀት እና እጹብነት ለማጉላት ነው። በምድር ላይ ሆነን እግዚአብሔርን ያወቅነው ወይም ልናቀው የምንችለው እግዚአብሔር በገለጠልን መልኩ ማለተም ውስን አእምሮአችን ሊሸከም ወይም ሊረዳ በሚችለው መጠን ስለሆነ ነው።

<u>ሚሥጢረ ሥጋዌ፡</u>

የሚሥጢረ ሥጋዌ ትርጉም

የአምላክ ሰው መሆን መሆን መሠረታዊ የሰው ለጅ የመዳን ዋስትና የተገኘው ስለ ሆነ የሰው ልጅ እንዲሁ በቀላሉ የሚታይ አይሆንም ለመገንዘብም በቀላሉ የሚችል ባለመሆኑ ሚሥጥር ሊባል ይግባዋል ። በተለይም በሰው ሥጋዊ እውቀት ሊሆን አይቸል ምክንያቱም ሰውበራሱ ብቻውን ጎዶሎ እውቀቱም ውስን መሆኑን ያመለክታል።

ዓለም ሳይፈጠር ከአብ ባሕርይ ዘእም ባህርይ የተወለደ የእግዚአብሔር ቃል ወልድ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እኛን ከመርገም ከፍዳ እና ከዘላላም ኩነኔ ለማዳን በኋለኛው ዘመን ከእመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወለደ። ከኃጥያት በስተቀር ሰው የሚሰራውን ሁሉ እየሰራ ብእየጥቂቱ አደገ። ስለኛ ህግን ሁሉ ፈጸመ (ገላ 4፥ 4-6) ። ከዚህም በኃላ ስለኛ መከራን ተቀበለ፣ ተሰቀለ፣ ሞተ፣ ተቀበረ፣ በሦስተኛውም ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሣ፣ በተነሣም በአርባኛውም ቀን

ወደሰማይ ዐረገ፣ በአባቱ በአብ ቀኝ ተቀመጠ። ዳግመኛም በክብር እና በምስጋና በሕያዋን እና በሙታን ላይ ለመፍረድ ይመለሳል ለመንግስቱም ፍጻሜ የለውም (ዳን 7፥ 13-15) ብለን እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ እና ሰው መሆኑን በማመን እንመሰክራለን።

ከሥላሴ ከሦስቱ አካል ወልድ (ቃል) ሰው ሲሆን የአምላክ ባህሪ እና የሰው ባህሪ ከሁለት ባህሪ በተዋህዶ አንድ ሆነ። ይህም ማለት ከኃጥያት በስተቀር የመለኮት ባህሪ ለሰው የሰውም ባህሪ ለመለኮት ሆነ ማለት ነው ።

የእግዚአብሔር መለኮታዊ ባሕርይ እና የሰው ባሕርይ

<u>መለኮታዊ አካል</u>	<u>ሥጋዊ አካል</u>	<u>መለኮታዊ ባሕርይ</u>	<u>ሥጋዊ ባሕርይ</u>
➢ ረቂቅ	➢ ግዙፍ	➢ ፈተኛና ኃለኛ	➢ መፈጠር
➢ የማይጨበጥ	➢ ውስን	➢ መጀመሪያ እና መጨረሻ	➢ ቀስ በቀስ ማደግ
➢ የማይዳሰስ	➢ የሚዳሰስ	➢ ፈጣሪነት	➢ ማልቀስ
➢ እሳታዊ	➢ የሚጨበጥ	➢ ሁሉን ማድረግ መቻል	➢ መራብ
➢ ምሉዕ የሆነ		➢ ዘላለማዊነት	➢ መጠማት
		➢ የማይሞት	➢ መድከም
		➢ የማይለወጥ	➢ ማንቀላፋት
		➢ የማይታመም	➢ መጨነቅ
		➢ የማይራብ	➢ መውደቅ
		➢ የማይጠማ	➢ መነሳት
		➢ የማይደክም	➢ መሞት

የቤተክርስትያን አባቶች ይህንን ረቂቅ የሆነ ክንዋኔ እንዲህ ይሉታል። እንቲአሁ ለቃል ኮነ ለሥጋ ወእንቲአሁ ለሥጋ ኮነ ለቃል። ሲተረጎም የቃል (የወልድ) የባሕርይ የሆነው ሀብት ለሥጋ ሆነ የሰውም የባሕርይ የሆነ ሀብት ለቃል (ለወልድ) ሆነ ማለት ነው። ይህም ታድያ በተዋህዶ። እግዚአብሔር ወልድ ከመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሲወለድ ከላይ የተጠቀሰው መለኮታዊ ባሕርይ ከሥጋዊ ባሕርይ ጋር ተዋህደ። ይህም በመሆኑ እግዚአብሔር ወልድ የሰው ሥጋ በመንሳቱ በሥጋ ታየ፣ ቀስ በቀስ አደገ፣ የናቱን ጡት ጠባ፣ አለቀሰ፣ ተራበ፣ ተጠማ፣ ደከመ፣ አንቀላፋ፣ ይህ ጽዋ ከኔ ትለፍ በማለት ተጨነቀ፣ ተመላለሰ፣ ተሰቀለ ሞተ ተቀበረ። ሥጋ ደግሞ የእግዚአብሔር ወልድን (የመለኮትን ባሕርይ) በመዋሀዱ የሞተው ሥጋ በሦስተኛው ቀን ሞትና መቃብርን ድል አድርጎ ተነሳ፣ ሥጋ በመለኮት በርቀት ወደሲኦል ወርዶ ነፍሳትን ነጻ አወጣ፣ ሥጋ በመለኮት እየታየ ወደሰማይ ዓረገ፣ ሥጋ በመለኮት ከአብ ቀኝ ተቀመጠ፣ ሥጋ በመለኮት መራብ፣ መጠማት፣ ማንቀላፋት፣ መሄድ መምጣት አቆመ፣ ሥጋ በመለኮት ምሉዕ ሆነ፣ ሥጋ በመለኮት ሁሉን ቻይ ሆነ፣ ሥጋ በመለኮት ፈተኛና መጨረሻ ሊባል በቃ። ይሄ ሊሆን የቻለው በተዋህዶ፤ የቃል ገንዘብ ለሥጋ የሥጋ ገንዘብ ለቃል በመሆኑ ነው።

የቃል (ወልድ) ሥጋ መሆን ሁለት ልደት እንዲኖረው ሆኗል። ቅድመ ዓለም ከባሕርይ አባቱ ከአብ ያለ እናት፥ ከ አምስት ሺ አምስት መቶ አመት በውህላ፤ ድህረ ዓለም ካለ አባት ከመቤታችን ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ ተወለደ።

<u>ሚሥጢረ ትንሣኤ ሙታን፡</u>

የክርስትና ትምህርት ከሁሉም ልዩ የሚያደርገው ከዚህ ሕይወት ሌላ ሕይወት አለ ብሎ ማስተማሩ ነው የቤተ ክርስቲያናችን አንቀጸ ሃይማኖት የሚያስረዳው ይህንን ነው “በኋለኛው ዘመን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በጌትነትና በምስጋና ተመለሶ

ይመጣል። በዚያም ጊዜ የሞቱት ሰዎች ሁሉ ይነሳሉ ከተነሡ በኋላ መልካም የሠሩ ወደዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ ክፉ የሠሩ ወደ ዘላለም ኩነኔ ይሄዳሉ"። (ማቴ 25፥46)

የትንሣኤ መሠረቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ ከእንግዲህ ወዲህ ሞት በማይገዛው አካል መነሳቱ ነው። በእርሱ ያመኑ ሁሉ በጥምቀት የተቀበሉትን ዐረቦን (መያዣ) የሚገልጸውን የትንሳኤ ክብር ይቀዳጁ ዘንድ የተዋረደው ሥጋቸው ተለውጦ መድኅኒታችን ከሞት የተነሳበትንና ያረገበትን ዳግመኛም ተመልሶ የሚመጣበትን አካል በሚመስል አካለ ሥጋ ይነሣሉ። በሌላ አነጋገር ትንሣኤ ሙታን ማለት ተለያይተው በተለያየ ሥፍራ ይኖሩ የነበሩ ነፍስና ሥጋ እንደገና ተዋሕዶ መነሳትና ከሞት በኋላ በነፍስና በማይፈርስ በማይበሰብስ በተለየ ሕይወት መኖር ማለት ነው። ሰው ሞቶ በስብሶ አፈር ትብያ ከሆነ በኋላ እንዴት ይነሳል? ለዚህ መልስ የሚሆነው ሰው በመጀመርያ ሲፈጠር በዘልዓለማዊ ሕይወት መፈጠሩን እንደሆነ አንርሳ (ዘፍ. 2፥7) ። አሁንም እግዚአብሔር ሰውን ለዘለዓለም ያኖረዋል ። ይህን የምናምነው ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም የሚለውን ሃይማኖታዊ እምነት ነው የምንለው። ስለዚህ በሙታን ትንሣኤ እናምናለን ተስፋም እናደርጋለን ስንል በእግዚአብሔርና በተስፋውም ቃል በመተማመን ነው። (ዮሐ. 5፥ 24 -29)

መፀሐፍ ቅዱስ ስለትንሣኤ ሙታን እንዲህ ሲል ያስተምራል።

- "ኢየሱስ እንደሞተና እንደተነሣ ካመንን እንዲሁም በኢየሱስ ያንቀላፉትን እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋልና"(1ኛ ተሰሎንቄ 4፥14)
- "ሙታንም ሕያዋን ይሆናሉ ሬሣዎችም ይነሳሉ በምድር የምትኖሩ ሆይ ጠልህ የብርሃን ጠል ነውና ምድርም ሙታንን ታወጣቸዋለችና ንቁ ዘምሩ"(ት/ኢሳ 26፥19)
- "በመቃብር ያሉት ሁሉ ድምጹን የሚሰሙበት ሰዓት ይመጣል መልካምም ያደረገ ለሕይወት ትንሣኤ ክፉም ያደረገ ለክፉ ትንሣኤ ይወጣሉ"(ዩሐ. 5፥28)

<u>ነገረ ቤተክርስትያን፡</u>

ቤተክርስትያን በጥንቱ በጽርዕ ቋንቋ **<u>ኤክለሲዓ</u>** ማለት ሲሆን ትርጓሜውም ለአንድ አላማና ሥራ የተመረጡ እና የተጠሩትን ማኅበር ወይም ጉባኤን ያመለክታል። የተልየ ጉባኤ ይባላል የምጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ቢገባበት

ቤተክርስትያን በሁለት ይከፈላል

1. የጌታችን የመዳሂኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋው እና ክብር ደሙ የሚፈተትበት፣ ቅዳሴ አምልኮ የሚከናወንበት ሕንፃ ቤተክርስትያን ይባላል።
2. እያንዳንዱ ምእመን በቅድት ሥላሴ ሦስት አካል ስምና ግብራት እና የመለኮት አንድነትን ፣ ጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ከድንገል መወለዱን አዳኝነቱን፣ ጌትነቱን፣ ሞቱንና ፣ እና ትንሣኤውን የሚያምኑ ቤተክርስትያን ይባላሉ። ይህ በሁለተኛው የተጠቀሰው ቤተክርስትያን **<u>ድል አድርጋ ነጻ የወጣች ቤተክርስትያን</u>** እና **<u>በፈተና ላይ ያለች ቤተክርስቲያ</u>**ን በመባል በድጋሚ በሁለት ይከፈላል። ታድያ አከፋፈሉ በቦታ እና በባህርይ ነው እንጂ በመንፈስ ቅዱስ ሱታፌ በመኃበራዊ አንድነታቸው አይነጣጠሉም።
    - **ድል አድርጋ ነጻ የወጣች ቤተክርስትያን፡** ማለት ይህንን ዓለም ድል ነስተው በሰማይ በአጸደ ነፍሥ ያሉት የቅዱሳን ማህበር ማለት ነው።
    - **በፈተና ያለች ቤተክርስትያን፡** ማለት ደግሞ ቢዚህ በምድራዊ አለም ውስጥ የምንኖር በተለያየ ፈተና ውስጥ እየወደቅን እና እየተነሳን የምንገኝ ምእመናን ማለት ነው። እያንዳንዱ ክርስትያን የመንፈስ ቅዱስ ማደርያ ስለሆነ ነው (1ኛ ቆሮ 6፥ 12-20)

ነገር ግን ከዚህ አለም በሞት ተለይተው በአጸደ ነፍስ ያሉት ቅዱሳን እና እኛ በክርስቶስ ክርስትያን የተባልን ምእመናን በጸሎት ሕብረት እናደርጋለን። ለዚህም ነው ሕያውያን ለሙታን ሙታንም ለሕያውያን የሚጸልዩት። (ራእይ 6፥ 10)

በመጀመርያ ላይ የተጠቀሠው የቤተ መቅደስ ሕንፃ ቤተክርስትያን ምሳሌነቱ የክርስቶስን አካል ያሳያል (ዩሐ. 2፥ 18-22።) እርሱም እንደ ሕያው ድንጋይ ነው። እኛም አባላቱ እንደ ሕያው ድንጋዮች በመንፈሳዊ ሕንፃ ውስጥ ተገንብተናል። ሐዋርያው ቅዱስ ጴጥሮስ እንዳለው፦ “እናንተ ደግሞ እንደ ሕያዋን ድንጋዮች ሆናችሁ በኢየሱስ ክርስቶስ ለእግዚአብሔር ደስ የሚያሰኝ መንፈሳዊ መሥዋዕትን ታቀርቡ ዘንድ ቅዱሳት ካህናት እንድትሆኑ መንፈሳዊ ቤት ለመሆን ተሰሩ” (ጴጥ. 2፥ 4-5 ፤ ኤፌ. 2፥ 20-22.)

ሚሥጥራተ ቤተክርስትያን

ሰባቱ ሚሥጢራተ ወይም ሥራዓተ ቅዳሴ ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፤

1. ሥርዓተ ጥምቀት
2. ሥርዓተ ሜሮን
3. ሥርዓተ ቁርባን
4. ሥርዓተ ክህነት
5. ሥርዓተ ተክሊል
6. ሥርዓተ ንስሓ
7. ሥርዓተ ቀንዲል

ሚሥጢረ ጥምቀት፡

ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር የጸጋ ለጅነት የምታስጥብት ወይም የዳግም ልደት የሚገኝበት ሥርዓት ጥምቀት ይባላል

የጥምቀት ትርጉም - መነከር፣ መዘፈቅ፣ መቀበር ውሃ ውስጥ ገብቶ መውጣት፣ ማለት ነው።

ሚሥጢር መባሉ - በዕለተ ዓርብ ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ከቀኙ ጎን የፈሰሰው ማየ ሕይወት ምሳሌ በሆነው ውሃ አማካኝነት ከሥላሴ ልጅነት የምናገኝበት ስለሆነ ነው። ይኸውም በዓይን የማይታይ ስውር ክንዋኔ ነው። ይህ ስወር ክንዋኔ የሚፈፀመው ካህኑ በዓይን የሚታየውን ውኃ በተገቢ እቃ አድርጎ ለጥምቀት የተመደበውን ሥርአተ ጸሎት አከናውኖ ሥራተ ቅዳሴውን ። ካደረሰ ብኋላ በአብ ስም በውልድ ስም በመንፈስ ቅዱስ ስም ብሎ በባረከው ጊዜ ውኃው ተለውጦ በዕለተ ዓርብ ከጌታችን ከመድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከቀኝ ጎኑ የፈሰሰ ማየ ሕይወት ይሆናል። ሰውም ከዚያ በኋላ ተለውጦ ማየ ሕይወት በሆነው ውኃ ሲነከር ከክርስቶስ ሞትጋር ይተባበራል ከውኃውም ሲወጣ ከክርስቶስ ትንሣኤ ጋር ይተባበራል፣ ከፍዳ ይነጻል፣ ከዳቢሎስ ቁርኝነት ይላቀቃል፣ ሃብተ ክርስትናን እና ከሥላሴ ልጅነትን ያገኝበታል። (ሮሜ 6፥ 3-11) መስተካከል ያስፈልገዋል

የጥምቀት መሰረት - ጌታችን መድሃኒታችን እየሱስ ክርስቶስ ከሞቱና ትንሣኤው በሥኋላ ለሐዋርያት ያዘዘው ትእዛዝ ነው። “እንግዲህ ሒዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ፣ በወልድ እና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው” (ማቴ. 28 ፥ 19-20)

ጥምቀት ያስፈለገበት - የመጀመሪያው አባታችን አዳም በሠራው ኃጢአት ልጅነቱ ስለተወሰደበት ሰው ሁሉ የሞት ፍርድ ተፈርዶበት ከፍዳና ከመርገም በታች ሆኖ ይኖር ነበር። ስለዚህ ሰው ሁሉ ሁለተኛ ከውሃና ከመንፈስ መወለድ ያስፈልገዋል። ሰው ከውሃ እና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ከእግዚአብሔር ተወልዶ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ይገባ ዘንድ አይችልም። ከሥጋ የተወለደ ሥጋ ነው ከመንፈስ የተወለደ መንፈስ ነው ስለዚህ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጥምቀትን አደረገልን። (ማቴ 28፥ 19 ፤ ዩሐ. 3፥ 3-6.)

የጥምቀት አንድነት - ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ለማዳን አንዱ የመስቀል ሞትን ሞቶ በሦስተኛው ቀን ተነስቶል። እኛም በጥምቀት ሞቱን በሚመስል ሞት እና ትንሳኤውን በሚመስል ትንሳኤ አንደየ ሞተን በመነሣት እንተባበራለን። ጥምቀት የሞት እና ትትንሣኤ ምልክት እንደመሆኑ መጠን ይልቁንም የክርስቶስ ሞት እና ትንሣኤ እንደማይደገሙ ሁሉ ጥምቀትንም አይደገምም። ይህ ታድያ የጥምቀት አንዲት መሆን ያስገነዝበናል። ወይም ሰው በስጋ ከስጋ ወላጆቹ የሚውለደው አንድ ጊዜ እንደመሆኑ መጠን ክርስቲያን በጥምቅት አንደየ መወለድ በቂው ነው

ሚሥጢረ ሜሮን፡

ሜሮን የሚለው ቃል የግሪክ ሲሆን ትርጓሜውም ቅዱስ "ቅብዐት" ማለት ነው። በተቀደሰ ቅብዐት መቀባት በኦሪት ሕግ የተደነገገ ነው። ካህናት የመቅደሱን ንዋያተ ቅድሳት በተቀደሰው ቅብዐት እንዲቀቡ ተጽፏል (ዘፀ. 30፥ 22-38)። በአዲስ ኪዳን ሜሮን ማለት ከጥምቀት ቀጥሎ የሚፈጸም መንፈስ ቅዱስ የሚያሠጠን እና በመንፈስ ቅዱስ መታተማችንን የሚያረጋግጥልን ታላቅ ሚሥጢር ነው። ጌታችን ከዮርዳኖስ ወንዝ ተጠምቆ ሲወጣ መንፈስ ቅዱስ እንደ ወረደ የባሕርይ ልጅነቱ እንደታወቀ እንዲሁም ምዕመናን ሲጠመቁ በሚሥጥረ ሜሮን የጸጋ ልጅነት ማግኘታቸውን ይረጋገጣሉ። ተጠማቂዎች በሚሥጥረ ጥምቀት እና ሜሮን አማካኝነት ከክርስቶስ ጋር አንድ ይሆናሉ፣ በመንፈስ ቅዱስም ታትመው አዲስ የሆነውን የመንፈስ ቅዱስ ሕይወት ይጀምራሉ። ይህም ማለት በዚያው ሥአት የሰማያዊ ዜግነት ሙበት ያገኛሉ ማለት ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስም ስለዚህ ጽፏል "በክርስቶስ ከእናንተ ጋር የሚያጸናንና የቀባን እግዚአብሔር ነው፥ ደግሞም ያተመን የመንፈሱም መያዣ በልባችን የሰጠን እርሱ ነው" (2ኛ ቆሮ. 1፥21-22)።

ቤተክርስትያን ከክርስቶስ በቀር ሌላ መሥራችና መሠረት ስለሌለ፤ የሚሥጥረ ሜሮንም መሠረትም እንዲሁ አምላካችን ኢየሱ ክርስቶስ ነው። ምክንያቱም መንፈስ ቅዱስን የሚሰጥ እና የሚያሰጥ እርሱ ብቻ ነው። (ዩሐ. 3፥16) ክርስቶስ ለሐዋርያት የሚያጸና እና የሚያጽናና ወደ እውነት ሁሉ የሚመራቸው መንፈስ ቅዱስ እንደሚልክላቸው ተስፋ ሲሰጣቸው እንረዳለን።

ዛሬ በቤተክርስትያን ውስጥ የሚደረገው እና የሚታየው በቅብዐ ሜሮን ሥርዓት አማካኝነት የማይታየው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ ይሰጣል። ለሲህም ነው በሚታየው ሥርዓት የማይታየው የጸጋ ልጅነት ስለሚገኝ ሚሥጥር የተባለው። ከውኃ እና ከመንፈስ የተወለደ ክርስትያን ማለትም በሚሥጥረ ጥምቀት እና በሚሥጥረ ሜሮን ሥርዓት ዳግም ከእግዚአብሔር በጸጋ ልጅነትን ያገኘ ክርስትያን የመንፈስ ቅዱስ ሀብታት ያድርበታል። የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የጥበብ እና የማስተዋል መንፈስ፣ የእውነትና የኃይል መንፈስ፣ የዕውቀት እና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ፣ ያርፍበታል" (ኢሳ. ፲፥ 2) ።

ሚሥጢረ ቁርባን፡

ቅዱስ ቁርባን ማለት ጌታችን መድሃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በስቅለቱ ዋዜማ ስለ እናንተ የሚቆረሰው ሥጋዬና የሚፈሠው ደሜ ይህ ነው ለመታሰቢያዬ ይህን አድርጉት ብሎ የሠራልን ሥጋውንና ደሙን ከጥምቀት በኋላ ከኃጥያት ርቀን በንጽሕና ሆነን በመቀበል ከጌታችን ጋር ኅብረት የምናደርግበት ድህነትም የምናገኝበት ታላቅ ሥጦታ ነው።

ለዚህም መሠረቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። "የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ" (ዮሐ. 6፥ 35) ሰው ሁሉ የጌታን ሥጋ እና ደም ካልበላና ካልጠጣ በስተቀር ከክርስቶስ ጋር አንድነት አይኖረውም። የዘላለም ሕይወትም አያገኝም። ማስረጃችንም የጌታ የራሱ ቃል ነው። "ሥጋዬን ያልበላ ደሜንም ያልጠጣ የዘላለም ሕይወት የለውም" (ዮሐ. 6፥ 53-54.) ብሎ ተናግሮአል። ይህንንም በደንብ እዚያው የዮሐንስ ወንጌል 6፥ 51-59 ሲያብራራልን እንዲህ በማለት ነበር "ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ

እኔ ነኝ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል እኔም ስለ ዓለም የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው.....እውነት እውነት እላችኋለው የወልደ እጓለ እመሕያው ክርስቶስ ሥጋን ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም። ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው እኔም በመጨረሻ ቀን አስነሳዋለሁ። ሥጋዬም እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነውና።

ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ። ሕያው አብ እንደላከኝ እኔም ከአብ የተነሣ ሕያው እንደምሆን እንዲሁ የሚበላኝ ደግሞ ከእኔ የተነሣ ሕያው ይሆናል።(ዮሐ. 6፥5-59)

ሚሥጥረ ቁርባን የተባለበት ዋና ምክንያት በኅብስቱ እና በወኑ ፍሬ አማካኝነት የመናገኘው የጌታችን የመድሃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ሥጋ እና ቅዱስ ደም ስለሆነ ነው። የመለወጡ ሥርዐት የሚከናወነው ካህኑ ኅብስቱን በጸሐል ወይኑን በጽዋ አድርጎ በጸሎተ ቅዳሴ በባርከው ጊዜ ኅብስቱ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋ ወይኑም የጌታቸን የኢየሱስ ክርስቶስ ደም ይሆናል። ይህ ረቂቅ መለኮታዊ አሠራር በዓይን ሳይሆን በእምነት ብርሃን የሚታይ ስለሆነ ሚስጥር ተባለ። ለዚህም ዋና ምሥክር የሚሆነን በስቅለቱ ዋዜማ በጸሎተ ሐሙስ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ አዲስ ቃልኪዳን ሲመሠርት ለደቀመዛሙርቶቹ የቀረበውን ኅብስት እና ወይን እንዲ በማለት ነበር የሰጣቸው " ኅብስቱን አንስቶ ባርኮ ቆርሶም እንካችሁ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንስቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፦ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጥያት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው" (ማቴ. 26፥ 26-28)። ከዚህ የምንረዳው በዓይን የሚታየው ኅብስት እና ወይን ተለውጦ የክርስቶስ ክቡር ሥጋው ቅዱስ ደሙ መሆኑን ነው።

<u>ሚሥጢረ ክህነት፡</u>

ሚሥጥረ ክህነት ማለት በእግዚአብሔርና በምእመናን መካከል ተገኝተው የእግዚአብሔርን ፈቃድና ትእዛዝ ለመፈጸም እና ለማስፈጸም፥ አማኞችን ለመጠበቅ፥ ለመምከርና ለማስተማር፥ እንዲሁም ለመጸለይ እና ለመባረክ፥ በጠቅላላው ምሥጢራተ ቤተ ክርስትያንን ለመፈጸም እንዲችሉ ለማድረግ በእግዚአብሔር ጥሪ የሚድርሳቸው ሰዎች በጳጳሳት ጸሎት የሚሰጥ መንፈሳዊ ማዕረግን እና ሥልጣንን የሚያስገኝ ከፍተኛ ሚሥጢር ነው። ያለዚህ ሚሥጥር ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ሚሥጥራት ሊከናወኑ ስለማየችሉ ይህ ሚሥጥር በቤተ ክርስቲያን ታላቅ ሚሥጥር በመባል ይታወቃል

ክህነት የሚለው ቃል "ካህን" ከሚለው ቃል የተገኘ ሲሆን፤ ትርጓሜውም "አገልጋይ" ማለት ነው። ክህነት የሚለው ቃል መንፈሳዊ ማእረግ እና ሥልጣኑን ሲያመለክት ካህን የሚለው ቃል ደግሞ በመንፈሳዊ ማእረግ እና ሥልጣን የከበረውን ሰው (አገልጋይ) ያመለክታል።

የካህናት ሦስት ዐበይት ተግባራት እንርሱም፤

1. "ሂዱና አስተምሩ" የሚለው ትእዛዝ ትምህርተ ወንጌል ለሰው ልጆች ከሁሉ በፊት የሚያስፈልግ መሰረታዊ ነገር መሆኑን ይስረዳናል (ማቴ. 28፥ 19-20) ። ስለዚህ የካህን የመጀመሪያው ተግባር ጸሎትና ቃለ እግዚአብሔርን ለማስተማር መትጋት ነው። ስለዚህ ነው ሐዋርያት ሌላውን ሥራ ለሌላ ሰጥተው "እና ግን በጸሎትና ቃሉን ለማገልገል እንተጋለን" ይሉት (የሐዋ. ሥራ 6፥ 1-4)።
2. ሕዝብን ከኃጢያት ወደንሥሐ መመለስና የቅድስናን ጎዳና ማስተማር ነው። (ዮሐ. 20፥23 ፤ 1ኛ ጴጥ. 1፥17)። ይህም ማለት ሚስጥራተ ቤተክርስትያንን መፈጸምና መንፈሳዊ አገልግሎትን ለምእመናን ሁሉ እንዲዳረስ ማድረግ ነው።
3. በጎቼን ጠብቅ፥ ግልገሎቼን አሠማራ የተባለው ትእዛዝ ነው (ዩሐ. 21፥ 15-17)። መንጋውን የመጠበቅ እና የማስተዳደር ሥልጣን ለጳጳሱ ብቻ የተሰጠው ሳይሆን እያንዳንዱ ካህን በየአጥቢያው የሚገኙትን ምእመናን ከጎዶሎ አሠተምሮ እንዲሁም ከዲያብሎስ ወጥመድ እንዲድኑ በየጊዜው ሳይሰለቹ ማስተማርና መምከር መገሠፅና መምከር ያስፈልጋል።

ሚስጥረ ክህነት ለተለዩ ስዎች ብቻ የሚሰጠ ሥራ ነው።

እግዚአብሔር ሥልጣነ ክህነትን ለተለዩ ብቻ መስጠቱን ለማመልከት ከአሥራ ሁለቱ ነገድ ከተሰበሰቡት በትሮች መካከል የአሮን በተር በተአመር ለምልማ እንድታብብ እና እንድታፈራአድርጓል። “ይአሮንን በትር ወደ ምስክሩ ፊት መልስ፤ ማጉረምረማቸው ከእኔ ዘንድ እንዲጠፋ እነርሱንም እንዳይሞቱ ለሚያምፁብኝ ልጆች ምልክት ሆና ትጠብቅ አለው” (ዘኍ. 17፥ 1-11) ።

በአዲስ ኪዳንም ሥልጣነ ክህነት ለተመረጡት ብቻ እንጂ አማኞች ለሆኑት ሁሉ ለወንዶችም ለሴቶችም አይሰጥም። ሐዋርያው ጳውሎስም የክህነት ሹመት ከመሰጠቱ በፊት በጥንቃቄ እንዲሆን በማሰብ መልካም ጠባያቸውና አኗኗራቸውን በማስመልከት መመረጥና መሾም ስለሚገባቸው ካህናት መመሪያ አዘጋጅቷል (1ኛ ጢሞ. 3 ፥ 1-13 ፤ ቲቶ 1፥ 6-9)። በዚህም ምክንያት ፈጥኖ እጆቹን በመጫን ካህናት እንዳይሾም ጢሞቴዎስን አስጠንቅቆታል (1ኛጢሞ. 5፥ 22) ዛሬም በቤተ ክርስትያናችን ይህ መመሪያ ተግባራዊ እንዲሆን በሕገ ቤተክርስትያናችን ተደንግጓል። ዲቁና ለመቀበል የሚፈልግ ሁሉ ከቃል ትምህርቱ ጋር ትምህርተ ሃይማኖትን፥ ሚሥጢራተ ቤተ ክርስቲያንን እና ትእዛዛትን ሁሉ በመጠኑም ቢሆን ማወቅ ይኖርበታል።

የክህነት ማዕረጋት በሦስት ይከፈላሉ።

ሐዋሪያዊ ትውፊት ያላቸው አብያተ ክርስትያናት ሦስት የክህነት ማዕርጋት አሏቸው።

1. የመጀመሪያው ደረጃ የኤጲስ ቆጶሱ ማዕርገ ክህነት ነው። የኤጲስ ቆጶሱ (ጳጳሱ) በሐዋርያት ወንበር ላይ የተቀመጠ ስለሆነ ሥልጣነ ክህነቱ ምሉዕ ነው። ሐዋርያዊ ትውፊት ያለው ሐዋርያትን መስሎ የክርስቶስ እንደራሴና (ተወካይ) ባለ ሙሉ ሥልጣን ስለሆነ በቤተክርስትያን ከፍተኛውን ማዕረግ ይይዛል። ቀሳውስትንና ዲያቆናትን የመሾም መብት እና ኃላፊነት የእርሱ ብቻ ነው። ሜሮን የመባረክ፥ አዲስ ሕንፃ ቤተክርስትያንንና ንዋያተ ቅዱሳትን የመባረክ ሥልጣን የኤጲስ ቆጶሱ ነው።
2. የሁለተኛው ደረጃ የቄሱ ነው። ከኤጲስ ቆጶሱ ቀጥሎ የሚገኘው ደረጃ የቄሱ ስለሆነ ክህነት ከመስጠት በስተቀር ስድስቱንም ምሥጢራተ ቤተክርስትያን ይፈጽማል። ለምእመናን የወንጌል ትምህርትና ምክር መስጠት መብቱና ግዴታው ነው። ለምእመናንም አበ ነፍስ በመሆን በመንፈሳዊ አባትነቱን መንፈሳዊ ልጆቹን ይጠብቃል በኃዘናቸውም በደስታቸውም ተካፋይ ይሆናል።
3. በሦስተኛ መአረግ ተመድቦ የሚገኘው ዲያቆኑ ነው። ዲያቆኑ ምሥጢራተ ቤተክርስትያንን ለመፈጸም መብት ባይኖረውም ቄሱና ኤጲስ ቆጶሱን ሚስጥራቱን በሚፈጽሙበት ጊዜ በመርዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል። ለምእመናን ወንጌልን በማስተማር እና ቅዱሳት መጻሐፍትን በማንበብ እንዲሁም ሌሎችን መንፈሳዊ አገልግሎት በመፈጸም የስራ ድርሻውን ይወጣል። ለጳጳሱ እና ለቄሱ መታዘዝም ከዋንኛ ተግባሩ አንዱ ነው።

<u>ሚሥጢረ ንስሐ</u>

አመሠራረት፤

ሚስጥረ ንስሀሐን የመሠረተ ራሱ ጌታችን ነው። የሰው ልጆች አዛኝ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ የሰው ልጆችን ኃጥያት ተሸክሞ በመስቀል ላይ ስለኛ ድህነትና ፈውስ እራሱን የተወደደ መስዋት አድርጎ ቅዱስ ሥራውን በመቁረስ እና ክብር ደሙን በማፍሰስ ከመርገመ ሞት እና ፍዳ ነጻ አውጥቶ አዲስ ሕይወት እና አዲስ የጽድቅ ጎዳና መሥርቶልናል። ይህንንም የድህነት ጸጋ በምሥጢረ ጥምቀት አግኝተነዋል። ከዚህ በኋላ ስለምንፈጽመው በደል ማስተሠርያ እንዲሆነን ለሐዋርያቱ እና እነርሱንም ለሚከተሉት ካህናት ሥልጣንን በመስጠት ምሥጥረ ንስሐን ለእኛ ጥቅምና ደኅንነት ሲል ይህንን ሥልጣን ለቤተክርስትያን አገልጋዮች ለጴጥሮስና ለሐዋርያት ተከታዮች ሰጥቷል። “የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሐለው

በምድር የምታስረው ሁሉ በሰማያት የታሰረ ይሆናል በምድርም የምትፈታው ሁሉ በሰማይም የተፈታ ይሆናል"(ማቴ. 16፥ 19)። እንደዚሁም ይህንን ሥልጣን ለጴጥሮስ እንደሰጠ ሁሉ ለሌሎች ሐዋርያት ሰጥቷቸዋል። "እውነት እላችኋለሁ በምድር የምታሥሩት ሁሉ በሰማይ ሰማይ የታሰረ ይሆናል ፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል" (ማቴ.18፥18)። የትንሣኤ ዕለት ለሦስተኛ ጊዜ ኃጢአት የማስተሠረይ ሥልጣን ሰጥቶ በመንፈስ ቅዱስ ሥጦታ አረጋግጦላቸዋል። "አብ እንደ ላከኝ እኔ ደግሞ እልካቸኋለው አላቸው። ይንንም ብሎ እፍ አለባቸውና መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ። ኃጥያታቸውን ይቅር ያላችኋቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው" (ዮሐ. 20፥ 21-23)

ንስሐን ለመፈጸም የሚያስፈልጉ አራት ነገሮች ። ሚካኤል ይህ ክፍል በጣም ሥራ ያፈልጋል ትንሽ ጊዜ ይጠይቃል ማለት በተለይ የንሥሐ ትምህር በደንብ መሠራት አልበት

1. ንሰሐ የሚገባ ሰው በቅድሚያ ንሰሐ መግባት ኃጢአት ሁሉ እንደሚሠረይና እንደሚደመሰስ ማመን አለበት። "ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንሰሐ ግቡ ተመለሱም" ተብሎ ተጽፏልና (የሐዋ. ሥራ 3፥19)
2. ንሰሐ የሚገባ ሰው የንሰሐ ኃዘን ሊኖረው ይገባል። ኃጥያቱን እያስታዋሰ ሰውንና ፈጣሪውን መበደሉን እያሰበ የሚያደርገው ኃዘንና ጸጸት ወደ ንሰሐ የሚወስድ እውነተኛ ኃዘን ስለሆነ ኃዘኑን እግዚአብሔር ይቆጥርለታል። "የሚያዝኑ ብፁዓን ናቸው መጽናናትን ያገኛሉና" (ማቴ. 5፥4) ተብሎ ተጽፎአልና። ንሥሐ ማለት ፀፀትን የሚያመለክት ቢሆንም ቁጭትና ቅንዓት የሞላበት የዓለማዊ ፀፀት ሳይሆን እውነተኛ ኃዘንና መመለስ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። ይህንን አስመልክቶ ሐዋርያው ጳውሎስ እደሚከተለው አስተምሮአል። "አሁን ለንስሐ ስላዘናችሁ ደስ ብሎኛል እንጂ ስላዘናችሁ አይደለም በምንም ከኛ የተነሣ እንዳትጎዱ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ አዝናችኋልና። እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ኃዘን ፀፀት የሌለበት ወደ መዳንም የሚያደርሰውን ንሰሐ ያደርጋልና የዓለም ኃዘን ግን ሞትን ያመጣል" (2ኛ ቆሮ. 7፥9-10)።
3. በሦስተኛ ደረጃ ንሰሐ የሚገባ ሰው ኃጥያቱን ሥል ጊዜጣነ ከህነት ላለው ካህን ይናዘዛል። ኑዛዜ ማድረግ በቅዱስ መጻሕፍት የታዘዘ ነው። "ከነዚህም ነገሮች በአንዲቱ በደለኛ ሲሆን የሠራውን ኃጢአት ይናዘዛል። ስለሠራውም ኃጥያት ለእግዚአብሔር የበደል መሥዋት ያመጣል....ካህኑም ስለ ኃጢአቱ ያስተሠርይለታል።....እርሱም ይቅር ይባላል" (ዘሌ. 5፥5-6 እና 10)። ይህ ጥቅስ ለካህን መናዘዝ እንደሚገባ ያስረዳናል። በአዲስ ኪዳንም የጌታ ወንድም ያዕቆብ የተባለውም ይህንኑ ያስተምረናል "እርስ በርሳችሁ በኃጢያታችሁ ተናዘዙ፥ ትፈወሱም ዘንድ እያንዳንዱ ስለ ሌላው ይጸልይ፤ የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች" (ያዕ. 5፥16)።
4. በአራተኛ ደረጃ ንሰሀ የሚገባው ሰው በእምነት፣ በኃዘን እና በኑዛዜ ኃጢያቱን ለካህኑ እና በስውር ለሚያየውና ለሚሰማው ለእግዚአብሔር ሲናዘዝ ከካህኑ ሁለት ነገሮችን ይቀበላል። እነርሱም ፍትሐትና ቀኖና ናቸው። ፍትሐት ማለት ከኃጥያት እሥራት የሚፈታበት ነው። ቀኖና ማለት ደግሞ ለኃጢአቱ ምክርና ተግሣፅ የሚያገኝበት የንሰሐ ቅጣት የሚቀበልበት የሚያመለክት ነው። ፍትሐት የሚሰጠው ካህኑ የንሰሐ ጸሎት ሥነ ሥራዓት ከፈጸመ በኋላ "እግዚአብሔር ይፍታ" በማለት ተናዛዡ ከኃጥያቱ እሥራት ይፈታል ከእግዚአብሔርም ይቅርታን ያገኛል።

<u>ሚሥጢረ ቀንዲል</u>

ትርጉም፡- "ቀንዲል" የሚለው ቃል ቀጥተኛ ትርጉሙ "በዘይት የሚበራ መብራት ወይም ማብሪያ" ማለት ሲሆን በመጽሐፈ ቀንዲል መሠረት በታመመው ሰው አጠገብ ሥርዓተ ጸሎቱ ሲፈጸም የሚበራውን መብራት ያመለክታል። ሚሥጢረ ቀንዲል ለሕሙማን ሁሉ አፈጸምም። እንደ ምድራዊ መድኃኒት ከሥጋ ደዌ ፈውስ ለማግኘት ብቻ የሚያስገኝ ተደርጎ መገመት አይገባም። የታመመው ሰው ምሥጢረ ቀንዲል የሚቀበለው የሥጋውን መዳን ብቻ ሳይመለከት የነፍሱን መዳን በማስቀደም ያሰበ እንደሆነ ነው። ስለዚህ ቀንዲል ከንሰሐና ከቅዱስ ቁርባን ጋር አብሮ የሚፈጸም እንጂ በተናጠል ብቻውን አይፈጸምም።

የሚሥጢረ ቀንዲል አመሠራረት፤

ይህ ሚሥጢር ጌታችን ለሐዋርያት ድውያንንም እንዲፈውሱ ሙታንን እንዲያስነሡ ለምጻሞችን እንዲያነጹ አጋንንትን እንዲያስወጡ የሕዝብንም ኃጥያት እንዲያስተሠርዩ ሥልጣን በሰጣቸው ጊዜ የተመሠረተ መሆኑን እናምናለን (ሙቴ. 10፥8፤ 18፥18) ። “አሥራ ሁለቱንም ወደ እርሱ ጠራ ሁለት ሁለቱንም ይልካቸው ጀመር፥ በርኩሳን መናፍስትም ላይ ሥልጣን ሰጣቸው፥...ወጥተውም ንስሐ እንዲገቡ ሰበኩ፥ ብዙ አጋንንትንም አወጡ፥ ብዙ ድውዮችንም ዘይት እየቀቡ ፈወሷቸው” (ማር. 6፥7 እና 12-13) ። እንግዲህ ከዚህ ጥቅስ የምንማረው ቅብዐ ዘይት እየቀቡ ድውያንን መፈወስ በጌታ ትእዛዝ በሐዋርያት የተጀመረ መሆኑን ነው። ስለዚህም ሚሥጢረ ቀንዲል ከሳባቱ ምሥጢራተ ቤተክርስትያን እንደ አንዱ ተቆጥሯል።

ምሥጢረ ቀንዲል እንደ አንድ ታልቅ የቤተ ክርስትያን ምሥጢር የተቆጠረበት ምክንያት ከሥጋ ፈውስ ጋር የነፍስም ጤንነት ማለት ከኃጢአት ደዌ የመፈወስም ኃይል ስላለው እንደሆነ ከላይ ተጠቅሶአል። ይኸንንም ከያዕቆብ መልእክት ለመገንዘብ እንችላለን። “ከእናንተ የታመመ ማንም ቢኖር የቤተ ክርስቲያንን ቀሳውስት ወደ እርሱ ይጥራ፤ በጌታም ስም እርሱን ዘይት ቀብተው ይጸልዩለት። የእምነትም ጸሎት ድውዩን ያድናል ጌታም ይስነሣዋል፤ ኃጢአትንም ሠርቶ እንደሆነ ይሠረይለታል” (ያዕ. 5፥14-15) ። ካህናት ዛሬም ይህንን በመከተል ሥርዓተ ጸሎቱን በማድረስና ቅብዐ ቅዱስን በመቀባት ህሙማንን ከሥጋና ከነፍስ ደዌ እንዲፈወሱ እግዚአብሔርን ይለምናሉ ኃጢያታቸውንም ይስተሠርዩላቸዋል። ይህም ሥርዐት ሚሥጢረ ቀንዲል ይባላል።

<u>ሚሥጢረ ተክሊል</u>

ምሥጢረ ተክሊል ማለት የሥርአተ ጋብቻ ጸሎት ሲሆን ሙሽራውና የሙሽራይቱ ጋብቻ ቃል ኪዳን በሃይማኖት የሚያጸና፥ የጋብቻን ግዴታ ሊያስወጣ የሚያስችል፥ በፍቅር የሚያስተሳስር፥ ዘላቂ አንድነትን የሚያሰጥ የጸሎተ ሥርአት ማልተ ነው ለዚህ ሥርአት ቅዱስ ቁርባን በጣም አስፈላጊ ምሥጢር ነው። ምክንያቱም የጋብቻ ሥርአት የቤተ ክርስቲያን ሚሥጢር ብቻ ሳይሆን ክብረ በአልም ስለሆነ ነው በተጨማሪም ቅዱስ ጋብቻ ሥርአት ለክርስቶስ እና ለቤተክርስትያን ፍቅርና አንድነት ምሳሌ ስለሆነ ታላቅ ሚስጢር መሆኑን ያስረዳናል (ኤፌ. 5፥31-32) ። ከዚህም በተጨማሪ ሚሥጢረ ተክሊል የረቀቀ ሚሥጢር ያሰኘው ሁለት ተለያይተው ያደጉ፥ ከተለያየ ቤተሰብ የተገኙ ወንድ እና ሴት በቤተክርስትያን ካህናት ቡራኬ እና ጸሎት፥ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋ እና ክቡር ደም በመታተም ከሁለት አካል አንድ የሚሆኑበት ሚሥጢር ስለሆነ ነው። “አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም። እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየውም” (ማቴ. 19፥ 1-9 ፤ ዘፍ. 1፥ 27፤ 2፥24 ፤ ዘዳ. 24፥1)።

ከፍጥረት ጀምሮ ቅዱስ ጋብቻ በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት ብቻ ተመሥርቶ እንደሚጸም ጌታችን አስተምሯል። “ያለ ዝሙት ምክንያት ሚስቱን የሚፈታ ሁሉ አመንዝራ ያደርጋታል፥ የተፈታችውንም የሚያገባ ሁሉ ያመነዝራል” (ማቴ. 5፥ 32) ።

በሚሥጢረ ተክሊል የከበረ ጋብቻ ሦስት አላማና ጥቅሞች አሉት፤

1. የመጀመሪያው እና ዋንኛው አላማ ልጆችን ለመተካት የሰው ዘርን ለማብዛት ነው (ዘፍ. 1፥27-28)።
2. ሁለተኛው የጋብቻ አላማና ጥቅም እርስ በእርስ መረዳዳት ነው። “እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም፤ የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት” (ዘፍ. 2፥ 18-25)። ለዚህ ነው አዳምን ከፋጠረ በውኃላ ሔዋንን የፈጠረለት። ሁለቱም ተጋግዘው እና ተደጋግፈው በመረዳዳት መኖር ይችሉ ዘንድ።
3. የጋብቻ ሦስተኛው አላማና ጥቅሙ ከአመንዝራነት ለመዳንና የሥጋ ፍትወትን ለመቆጣጠር ነው (1ኛ ቆሮ. 7፥ 8-9፤ ማቴ. 19፥ 10-12)።

ከላይ እንደተጠቀሰው ምሥጢረ ተክሊልን ከቅዱስ ቁርባን ጋር በመፈጸም የማይታየውን ታላቁን የእግዚአብሔር ጸጋ እንቀበላለን ። ከሥጋዊ አንድነት በላይ የሚሆነውን የመንፈስ አንድነት እና ፍቅርን በተጠናከረ ሁኔታ እናገኛለን። በተክሊል የሚገኘው ጸጋ ጋብቻን የተከበረና መንፈሳችንንም የተቀደሰ ያደርገዋል። “መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር፥ መኝታውም ንጹሕ ይሁን” ለመፈጸም ያስችላል (ዕብ. 13፥ 4)። ታድያ ይህ የተሰጠውን ጸጋ አክብሮ ለማቆየት በትዳር የከበሩ ሰዎች ሁልግዜ እየቆረብና ቃለ ወንጌልን እየሰሙ ለሕይወታቸው የሚያስፈልገውን መንፈሳዊ ምግብ ሊያገኙ ይገባቸዋል።

ክብረ ቅዱሳን

ክብረ ቅዱሳን ማለት የቅዱሳን ክብር ማለት ነው። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስትያን ሐዋርያዊት ቤተክርስትያን እንደመሆኗ መጠን ክርስቶስን መስለው፥ ስለወንጌል መስፋፋት የራሳቸውን ሳይሆን የጌታን ውለታ እና ፍቅር በማሰብ ብዙ መከራን የተቀበሉትን አባቶች እና አንስቶች ገድላቸውን በመጻፍ የሕይወታቸው ተመኩሮ አዲሱን ትውልድ እንዲያስተምር ቅዱሳንን ታከብራለች ትዘክራለች። ይህም ታድያ መጸሐፍ ቅዱሳዊ ነው "የእግዚአብሔርን ቃል የተናገሩአችሁን ዋኖቻችሁን አስቡ፥ የኑሮአቸውንም ፍሬ እየተመለከታችሁ በእምነታቸው ምሰሉአቸው" (ዕብ. 13፥7) ተብሎ ተጽፎልናል። ታድያ የቅዱሳን ክብር ከጌታችን ክብር እና አምሉኮ የተለየ መሆኑን መዘንጋት የለበትም። የሀይማኖት ራስ መደምደሚያው ወይም ጉልላቱ እራሱ አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። የድህነትም መሠረት እርሱ ብቻ ነው።

እግዚአብሔር ከኦሪት ጀምሮ ለሰው ልጆች ምሳሌ፥ አስተማሪ፥ መካሪና ተግሳፅ ሰጪ አድርጎ አስቀድሞ ነብያትን ከዚያም በውሐላ ሐዋርያትን ልኮልናል። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ያለው... "በሐዋርያትና በነብያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው" (ኤፌ. 2፥20) ።

ቅዱሳንን ማክበር የሕይወታቸውንም ፍሬ መርምሮ ፈለጋቸውን መገተል ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከት ያሰጣል። ምክንያቱም እውነተኛ ቅዱሳን ወደ እውነተኛው ጌታ የሚመሩ የብርሐን መቅረዝ ናቸውና። ይህንንም የሚያረጋግጥልን ሐዋርያው ጳውሎስ ነው "እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እኔን ምሰሉ" (1ኛ ቆሮ. 11፥1) ብሎ በድፍረት ተናግሯል እና። ከዚህ በተጨማሪ ክብር ለሚገባው ክብር መስጠት እንዳለብን ወንጌል ያዘናል። "ለሁሉ የሚገባውን አስረክቡ፤....ክብርን ለሚገባው ክብርን ስጡ።" (ሮሜ. 13፥7)

አምልኮ፥ ጾም፥ ጸሎት፥ እና ባሕላት

አምልኮ

አምልኮ ማለት መገዛት ማለት ነው:: ግዛቱም ለልጅ ልጅ ለሆነው ከዙፋኑ መቼም ለማይታጣው አምላክና አባት ለሆነው ለእግዚአብሔር ሁለንታዊ መገዛት ነው:: እግዚአብሔር አምላክና አባት ነው አምላክ ማለት ገዢ፣ ፈጣሪ፣ ኃይልና ሥልጣን ያለው ማለት ነው፤ እግዚአብሔር ማለትም በግእዝ ቋንቋ የዓለም ጌታ ማለት ነው:: የጉልበትን ክብር ሁሉ የሚወስድ የአንደበት ምስጋና ሁሉ የእርሱ የሆነ ተተካክሎት አምልኮውን የሚጋራው የሌለ በሰማይና በምድር አንድ እግዚአብሄር ነው፡ : (ኢሳ. 45፥23, ዘፀ. 15፥11 ዘዳ. 6፤4)

አምልኮ በታላቅ ክብር፣ በቅዱስ ፍርሃት፣ በተወደደ መንቀጥቀጥ ለአምላክነቱ መገዛት ሲሆን በአባትነቱ ቅርብነትም በፍፁም ግልጥነት በእግዚአብሔር ጆሮ መሰማት ነው:: እርሱ ድንቅ ተአምራትን ስላደረገ ብቻ ሳይሆን ስለማንነቱ የሚመለከ አምላክ ነው። የማንነቱ ምስጋናም እውነተኛ መገዛት ነው አሳቡ የማይከለከል ምክሩም የማይፈርስ ነውና ስለሚያደርግልን ነገር በፍጡር አይደገፍም (ኢዩ. 42፥2, ኢሳ. 40፥13, ኤፌ. 1፥11)

እግዚአብሄር አለ ብሎ ማመን አንድ ነገር ሲሆን ይህን እግዚአብሔር ማምለክም የእምነትና የቅድስና አካል ነው፡፡ ይህም ብቻ አይደለም አምልኮ በየዕለቱ የምንበላው እንጀራ ነው፡፡ አምልኮ በርኀራሄ /በአዛኝነት/ እና በማይለወጥ ፍቅር በዘለዓለም ምሕረቱ ለሚኖረው በመለኮት ውበት ላለውና ለሚኖረው ለእግዚአብሔር የማድነቅ የመመሰጥ ውዳሴ ነው፡፡

ጾም

ጾም ማለት መከልከል ማለት ሲሆን አላማውም ከምግብ ብቻ ሳይሆን ከዓይን አምሮት ከሥጋ ምኞት ከአለማዊ ነገሮች ሁሉ መከለከል እራስን በመቆጣጠር ከምድራዊ ሐሳብና ሥራ እራስን ነፃ በማውጣት ልባችንን ለእግዚአብሔር ቃል ብቻ የምናስገዛበት እና መልካም ሥራ ለመሥራት ኃይል የምናገኝበት መንፈሳዊ መሣሪያ ነው። ጾም እንደ ጸሎት ለክርስቲያናዊ ሕይወት አስፈላጊ ስለሆነ ጌታችን ክርስትያኖችን እንዴት በወንጌል ሥርዓት መጾም እንደሚገባ አስተምሯል (ማቴ. 6፥ 16-18) ጾም የሥጋን ምኞትና ምኞት በመከለል ለነፍስ ስንቅ የሚቋጠርበት በረከት የሚገኝበት ታላቅ ተግባር ነው። ለዚህም ነው መዝሙረኛው ዳዊት “ነፍሴን በጾም አደከምኳት” በማለት የተናገረው (መዝ. 34፥13)።

ታድያ ለምንድን ነው የጌታ ደቀመዛሙርት እንደ ፈሪሳውያን እና እንደ መጥምቁ ዮሐንስ ደቀመዛሙርት የማይጾሙት? የዚህ ጥያቄ መልስ ስለሁለት ነገር ነው። አንዱ ፈሪሳውያን እና የመጥምቁ ዩሐንስ ደቀመዛሙርት የሚጾሙት ጾም በብሉይ ኪዳን ሥርዓት ላይ የተመሠረተ ስለሆነ በአይነቱም፥ በዓላማውም፥ በይዘቱም የተለየ ነው። በተጨማሪም በዚህን ጊዜ ከብሉይ ወደ ሐዲስ ኪዳን የመሸጋገሪያ ወቅት ስለነበር ሐዋርያት ገና የሐዲስ ኪዳንን ትምሕርት በመቀበል ላይ ስለነበሩ ነው። ሁለትኛ እና ዋንኛ ምክንያቱ ደግሞ የጾም ዋና አላማን ያመለከተናል። ጾም ከምድራዊ ነገር እራሳችንን የምንከለከልበት እና ለመልካም ነገር እራሳችንን የምናስገዛበት ዋና ምክንያቱ ከጌታችን ጋር ያለንን ግንኙነት ለማጥበቅ ነው። ታድያ ለብዙ ዘመናት ሲጠበቅ የንበረ መሲሕ ክርስቶስ፥ ነብያቶች ለረጅም ጊዜ ሱባኤ የቆጠሩለት ሙሽራው እግዚአብሔር ወልድ ዘመናትን ቆጥሮ ከመቤታችን ከሥጋዋ ሥጋን ከነፍሷ ነፍስን ነስቶ በሐዋርያት ዘመን ተገልጦ ስለነበር የደስታ ጊዜ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ነው ጌታችን “ሙሽራው ከነርሱ ጋር እያለ ሚዜዎቹ ማዘን ይገባቸዋልን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚለይበት ጊዜ ይመጣል፤ በዚያን ጊዜ ይጾማሉ” (ማቴ. 9፥ 14-15) በማለት ያስተማረው።

ስለዚህ ጾም መለታዊ ትዛዝ ሲሆኣን መ] መጾም እንዳለብን በቅኖና ቤተክርስትያን አባቶች በሲኖዶሱው ደንዋል። በኢትዮጵያ አርቶዶስ ተዋህዶ ፀተክርስትያን ከሰባት ዓመት እድሜ ጀምሮ ያሉ ክርስትያኖች እንዲጾሙአቸው የተደነገጉ ሰባት አጹአማት አሉ። እነርሱም ከዚህ በትታች ተዘርዝረዋል፤

ሀ. የገና ጾም

ለ. የነነዌ ጾም

ሐ. ዓብይ ጾም

መ. የሐዋርት ጾም

ሰ. የፍልሰታ ጾም

ረ. የጋድ ጾም

ሸ. ሮብ አርብ ጽም ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ ክርስትያኖች በፈቃደኝነት ጾመ ጽዕን ወይም የግል ጾም መጾም ይችላሉ።

ጸሎት

ጸሎት ማለት ከእግዚአብሔር ካባታችን ጋር የምንነጋገርበት፥ ታላቅ በረከት እና ሐይል የምንቀበልበት፥ የሕይወት እንቆቅልሽን የምንፈታበት፥ እግዚአብሔር አባታችን እኛም ልጆቹ መሆናችንን የምናውጅበት እና ዲያቢሎስ ሴጣንን ድል የምንነሳበት ታላቅ መንፈሳዊ መሣርያ ነው። የእውነተኛ ጸሎት መነሻው ልብ ነው እንጂ አፍ አይደለም። ልብ በሌላ አሳብ ተይዞ አፍ ብቻውን ቢያነበንብ ጸሎቱ ዋጋ የለውም። እንደዚሁም በልቦናው የትዕቢትና የመመጻደቅ አሳብ ካለ እንደ ፈሪሳዊ ጸሎት ተቀባይነት አይኖረውም (ሉቃ. 18፥ 9-14)። የክርስትያን ጸሎት መሠረት ትሕትናና መታመን ነው። የእግዚአብሔርን ይቅርታና ምሕረት የመዳናችንንም ጸጋ የምናገኘው በእንዲህ አይነት ልቦና ወደ ክርስቶስ በመቅረብ ነው። ክርስትያናዊ ሕይወታችን በመንፈሳዊ ነገር የበለጸገ እንዲሆን የእምነት እና የጸሎት ተጋድሎ ይስፈልጋል። ስለዚህም አጥብቆ መጸለይና (ሉቃ. 11፥5-13) ሳይሰለቹ ዘወትር መጸለይ (ሉቃ. 18፥ 1-8) እንደሚገባ ጌታ በምሳሌ አስተምሮናል። ይልቁንም ደግሞ ወደ ፈተና እንዳንገባ ተግተን እንጸልይ፤ መንፈስ ዝግጁ ነው፤ ሥጋ ግን ደካማ ነውና (ማቴ. 26፥ 41)።

እንዴት መጸለይ እንዳለብን የጸሎቱም ይዘትና ሥርዓት ምን መምሰል እንዳለበት ያስተማረን እራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው (ማቴ. 6፥5-15)። ይህንንም ያደረገው ጸሎታችን እንደ አረማውያን ጸሎት እንዳይሆን ነው። በከንቱ ቃል በመደጋገም ብዛት እግዚአብሔር የሚሰማን እንዳይመስለን። ስለዚህ ነው ጌታ በወንጌል በየአደባባይ የቃል ድግምትን በማብዛት የሚጸልዩትን ፈሪሳዊያኖችን አይቶ "ስለዚህ አትምሰሏቸው፤ ሳትለምኑት አባታችሁ የሚያስፈልጋችሁን ያውቃልና። እንግዲስ እናንተ እንዲህ ጸልዩ" በማለት ጌታ የአቡነ ዘበሰማያት ጸሎትን ያስተማረው (ማቴ. 6፥7-15)።

አባታችን ሆይ ብለን እግዚአብሔርን ለመጥራት ሥልጣን ያገኘነው ከራሱ እግዚአብሔር ወልድ ሰው መሆን ምክንያት ነው። የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ በመሆን ላመኑ እና ለተቀበሉት የልጅነት ሙሉት ተሰጥቷቸዋል (ዩሐ. 1፥12)። በክርስቶስ አምነው በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም የተጠመቁ ሁሉ የሥላሴ ልጅነት አግኝተዋል። በሚሠጢረ ጥምቀት ባገኙት አዲስ ልደት እግዚአብሔርን አባት ብለው የሚጠሩበት የልጅነት መንፈስ ስላላቸው ግንኙነታቸው እንደ አባት እና ልጅ ነው (ሮሜ. 8፥15) ስለሆነም በጸሎት ጊዜ እኛ ያመንን እና የተጠመቅን ልዑል እግዚአብሔር "አባታችን ሆይ" ብለን እንጠራዋለን እንለምነዋለን፥ እናመሰግነዋለን።

<u>ባእላት</u>

በየዘመኑ እግዚአብሔር አምላካችን በነብያት፥ በሐዋርያት እና በመላዕክት አማካኝነት የሰው ልጆችን ከጥፋት መመለስ ለፈጸመው ከንውኖች መታሰቢያ ይሆኑ ዘንድ ባእላት በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ውስጥ ትልቅ ሥፍራ አላቸው። ስለሆነምለባእላት ሦስት ዐበይት ነጥቦችን ይይዛሉ።

1. የመጀመሪው አብይ ነጥብ የእግዚአብሔርን ቸርነት እና ይቅር ባይነት መዘከር ነው። እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ከነብያት ጊዜ አንስቶ እንከአሁን ድረስ ላሳየን ምህረት እና ቸርነት በማሰብ እነኛ አበየት የምህረት ክንውን የተደረገበትን ቀን እያስታወስን በተለየ መልኩ ለእግዚአብሔር አምላካችን ምስጋና እንድናቀርብ ይረዱናል።
2. በሁለተኛ ደረጃ እግዚአብሔር አምላክ ለሚታመኑበት እንዴት የምህረት ክንዱን እንደሚሰድ ከትውልድ እስከትስልድ ምስክር በመሆን ይረዳል። በየጊዜው የሚተካውም ትውልድ ለእግዚአብሔር መታመን እና መገዛት እንዴት ያለ ክብር እና ጸጋ እንደሚያስገኝ ይማርበታል መንፈሱን ያድስበታል።
3. በሦስተኛ ደረጃ ባእላት የመልካም ሥራ ቱሩፋት መዘከሪ፥ ማስታወሻ፥ እንደመሆናቸው መጠን፤ በበአል ጊዜ የተራቡትን በማብላት፥ የተጠሙት በማጠጣት፥ የታረዙትን በማልበስ፥ የታሰሩትንና የታመሙትን በመጠየቅ በጠቅላላው መልካም ሥራን በመስራት እንድናሳልፍ የሚረዱን አንዱ የመንፈሳዊ መሳሪያ ናቸው።

ታድያ ለበአሉ ምክንያት የሚሆኑ የተለያዩ ቢሆኑም በበአሉ ምስጋናን የሚወስድ የቅዳሴውም አምልኮ የሚቀበል አልፋና አሜጋ የሆነው አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነው።

ሥርዓተ ቤተክርስትያን

ሥርዓት የሚለው ቃል ሥራ ወይም ተግባርን የሚያመለክት ነው። ሥርዓት አንድን ክንውን እንዴት እና በምን መልኩ መተግበር እንዳለበት ግልጽ አድርጎ የሚያሳይ ጠቃሚ መሳርያ ነው። ለሥርዓተ ቤተክርስትያን መሠረቱ ሥርዓተ ደብተራ ኦሪት፥ሥርዓተ መቅደስ ኦሪት፥ ሥርዓተ ካህናተ ኦሪትና የመሳሰላው የብሉይ ኪዳን ሥርዓት ነው።

የደብተራ ኦሪት የመቅደስ ኦሪት አሠራር ለቤተክርስትያን ሕንጻ አሠራር ምሳሌነት አለው፤ ደብተራ ኦሪት መቅደስ ኦሪት መቅደስ በሦስት ክፍል ይሠራ እንደነበረ ሁሉ ቤተክርስትያንም ቅኔ ማኅሌት፥ ቅድስት፥ መቅደስ በሚል በሦስት ክፍል ትሠራለች። በደብተራ ኦሪት መቅደስ ኦሪት በግብር አምላካዊ አሥሩ ትእዛዛት የተጻፈበት ጽላተ ኪዳን ታቦተ ሕግ ይቀመጥበት እንደነበረ ሁሉ በቤተ ክርስትያንም ይኸው ሕጉ የተጻፈበት ጽላተ ታቦት ለመሠውያነት ይኖራል፤ መሠዋትም ይቀርብበታል። በብሉይ ኪዳን ይሠዋ የነበረው መሥዋዕት ቢያልፍም አቀራረብም ቢለወጥም ዛሬ በቤተክርስትያን አማናዊ መሥዋዕተ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ይሠዋል። በደብተራ ኦሪት መሥዋዕት አቀራረብ እንደነበረ ሁሉ ዛሬም በቅድስት ቤተክርስትያን ሕማሙን፥ ሞቱን፥ ትንሣኤውን፥ ዕርገቱን የተመለከተ የመሠዋዕት አቀራረብ ሥርዓት አለ ይህም "ሥርዓተ ቅዳሴ ሥርዓተ ቁርባን" እየተባለ ይጠራል።

ሥርዓት በራሱ ዶግማ አይደለም ነገር ግን ዶግማ የሆነውን ትእዛዝ እንዴት እና በምን መልኩ እንደምንፈጽም የሚገልጽልን ነው። ለምሳሌ በቅዱስ መጽሐፍ አምኮ ለእግዚአብሔር ማቅረብ እንደሚገባ ታዞአል። አምልኮ ዶግማ ነው። እንዴት ማምለክ እንደሚገባን ደግሞ አባቶች በሲኖዶሳቸው ሥርዓተ ቅዳሴን በቅኖና መልክ ሰጡን። እንደዚሁ ሁሉ በቤተክርስትያን ለሚከናወኑ ሚሥጥራት ሁሉ አባቶች በቅኖና መልክ እንዴት መፈጸም እንደሚገባ ሥርዓት አበጅተውላቸዋል። ሥርዓት ወደአንድ አይነት መንገድ ወደአንድ ልብ ያመጣል ለዚህም ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ነገር ግን ሁሉ በአገባብና በሥርዓት ይሁን" ብሎ የተናገረው (1ኛ ቆሮ. 14፥40)

ክርስትያናዊ መብትና ግዴታ

የክርስትና ህይወት የተመሠረተው ከራስ አልፎ ሌላውን ለማዳን፥ ሌላውን በመርዳት ላይ ነው። ይህንንም ለመፈጸም እንድንችል በመጀመርያ የኛ የራሳችንን መዳን መፈጸም ይኖርብና። ይህ ማለት ደግሞ የቤተክርስትያን አስተምሮን በሚገባ አጥንተን ማወቅ ከዚያም በኋላ ባወቅነው እውነት እንደተረዳነው መጠን በሕይወት መኖር አለብን። ይህንንም ማረግ እንድንችል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲ ሲል አዞናል "በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙቱ እንዲህ አለ፦ እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ" (ማቴ. 16፥24)። አንድ ሰው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ፈልጎ ለአገልግሎት በሚነሳበት ወቅት በመጀመሪያ ማድረግ እና መወሰን የሚገባው አገልግሎቱ የራሱን ክብር ለመግለጽ ሳይሆን የጌታን ክብር ለመግለጽ እንደሆነ በመወሰን ነው። ይህ ለክርስትያን ሰው የሚመራበት መንፈሳዊ ግዴታ ነው። አለበለዚያ በእግዚአብሔር ፋንታ የራሱን ክብር ነው የሚገልጸው ይህ ደግሞ የግዚአብሔርን አሳብ ሳይሆን የግል ፈቃድን በወንጌል ሽፍኖ በማቅረብ ሰውን ወደ ጽድቅ ጎዳና ከመምራት ይልቅ ወደጥፋት እና ወደ ፈተና እንድንመራ ያደርገናል። ስለዚህ አንድ አገልጋይ ለአገልግሎቱ ኃይል ማግኘት እንዲችል ትሁት በመሆን የራሱን ፈቃድ ለጌታ አሳልፎ ማስገዛት የመንፈሳዊ ግዴታው ያዛል። ለዚህ ነው ከመስቀል መሸከም በፊት "ራሱን ይካድ" የሚለው ትዛዝ የቀደመው። ከዚህ በተጨማሪ አንድ አገልጋይ ወደሰንበት ትምህርት ቤት ማህበር በሚቀላቀልበት ጊዜ በሚያገለግልበት አጥቢያ ቤተክርስትያን የተደነገገውን መብት እና ግዴታ ሊከተል ይገባዋል።